# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE
# OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


ሰላሳኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 49
ADDIS ABABA , 30 th July ,2024


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፭፻፶፬/፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በሦስተኛ ወገን የተሸከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የአረቦን ተመን እና የካሳ መጠን ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብየሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ገፅ ፲፭ሺ፯፻፴፪

ሰንጠረዥ.......................................ገፅ ፲፭ሺ፯፻፴፭


**CONTENT**


Regulation No.554/2024

Vehicle Insurance Policy Against Third Party Risks Premium Tariff and Amount of Compensation Fee Regulation ……………………………………Page 15732

……………………………………………….... Page 15735


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፶፬/፪ሺ፲፮ ዓ.ም

## በሦስተኛ ወገን የተሸከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የሚከፈለውን የአረቦን ተመን እና የካሳ መጠን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፱/፪ሺ፭ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በሦስተኛ ወገን የተሸከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የአረቦን ተመን እና የካሳ

## REGULATION No.554/2024

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR PREMIUM TARRIF AND AMOUNT OF COMPENSATION APPLICABLE TO VEHICLE INSURANCE POLICY AGAINST THIRD PARTY RISKS

This Regulation is issued by the Federal Democratic Republic of Ethiopia Council of Ministers pursuant to Article 4 sub article (4), sub article (5) Article 16 of Vehicle Insurance against third party Risks Proclamation No.799/2013.

1.Short Title

This Regulation may be cited as the "Vehicle Insurance Policy Against Third Party Risks Premium Tariff and Mount of

መጠን ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፶፬/፪ሺ፲፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ “አዋጅ” ማለት የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፱/፪ሺ፭ ነው፡፡

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ስር የተጠቀሱት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ፫.የአረቦን ተመን ክፍያ

ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፱/፪ሺ፭ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የአረቦን ተመን ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ “ሀ” በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

## ፬. የካሳ መጠን ክፍያ

ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር ፯፺፱/፪ሺ፭ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፭) በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የሚሸፈነው የካሳ መጠን ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ “ለ” በተመለከተው መሠረት ተሻሽሏል፡፡

## ፭.ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም የውሳኔ ቁጥር ፬/መስ፲፯/ው-፷፰/፪ሺ፫ የሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ

Compensation Fee Regulation No.554/2024.

## 2.Definition

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ “Proclamation” means Vehicle Insurance against third party Risks Proclamation No.799/2013;

2/ Definitions provided under Article 2 of the proclamation shall also be applicable to this Regulation.

## 3.Premium Tariff Fee

The amount of Premium Tariff Fee applicable to vehicle insurance policy against third party risks pursuant to sub article 4 of Article 4 of Proclamation 799/2013 shall be as prescribed in the schedule “A” attached hereto.

## 4.Compensation Fee

The amount of compensation to be covered by vehicle insurance policy against third party risks pursuant to sub article (5) Article 16 of the Proclamation shall be as prescribed in the schedule “B” attached hereto.

## 5. Inapplicable Laws

Council of Ministers Decision No. 4/መስ17/ው-68/2003 E.C dated April 28/2003

መድን ዋስትና የአረቦን መጠን እና የመድን ፈንድ ታሪፍን በተመለከተ ያስተላለፈው ውሳኔ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፮.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

አቢይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

E.C is hereby repealed.

6.Effective Date

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 30th day of July,2024

ABIY AHMED (Dr.)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA